**ORIGINAL ARTICLE**

# The Effects of learning through retelling strategy on reading Comprehension

***Banchiamlak Tsegaye*** [1] ***Marew Alemu***[2] **&** ***Agegnehu Tesfa***[3]

## *Abstract*

*The purpose of this study was to exmine the effects of reading-retelling strategy on reading comprehension. To achieve this purpose, a pretest-posttest quasi-experimental design was used. Students of sections were chosen at random from fourth-grade at a Meseret primary school in Gondar city in 2023. The study included 98 students, with 49 in each of two sections that were randomly assigned to the experimental and control groups. A reading comprehension exam was also used to collect data. Reliablity and validity of the data gathering tool were checked and found to be significant. Following the collection of pretest data, the experimental group were given reading comprehension lessons using a reading-retelling strategy, whereas the control group was taught reading comprehension by conventional methods for eight weeks (16 sessions). The data were analyzed with a one-way ANCOVA. The results showed a significant difference ($F(1, 96)=18.004$, $p <.001$, $\eta^2=.159$) between experimental and control groups. As a result, the study found that the reading-retelling strategy increased reading comprehension more than the control one. The findings also suggested that the reading-retelling strategy could be used as an alternative means of enhancing reading comprehension. It is hoped that this finding will inspire future scholars to investigate the strategy in a variety of scenarios.*

**Keywords:** retelling strategy, reading comprehension

## አሕጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዓላማ አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመር ነበር። የጥናቱ ንድፍ ቅድመ-ድኅረትምህርት ፈተና ባለቁጥጥር ቡድን ፍትነትመሰል (Quasi-Experimental pretest posttest control group design) ነው። ተሳታፊዎችም በጎንደር ከተማ በመሠረተ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት በ2015 ዓ.ም. ከአራት የመማሪያ ክፍሎች በእጣ የተመረጡ የኹለት ክፍሎች የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች በእጣ የተመረጡ ኹለት ክፍሎች በእያንዳንዳቸው 49 በአጠቃላይ 98 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል። የጥናቱ መረጃ አንብቦ በመረዳት ፈተና የተሰበሰበ ሲሆን አስተማማኝነቱና ትክክለኛነቱም ተፈትሾ ተገቢ ሆኗል። በፈተናውም የቅድመትምህርት መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ለሙከራ ቡድኑ አንብቦ በመተረክ ብልሃት፣ ለቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው ሥርዐተትምህርት መሠረት ለስምንት ሳምንታት (ለ16 ክፍለጊዜያት) በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ትምህርት ተሰጥቷል። በመጨረሻም የድኅረትምህርት መረጃው ተሰብስቧል። ከፈተናው የተገኘው መረጃ በቅድመትንተና ፍተሻዎች ተረጋግጦና የቅድመትምህርት ፈተናው ውጤት በአበር ተላውጦነት ቁጥጥር ተደርጎበት የድኅረትምህርት መረጃው በባለአንድ አቅጣጫ አበር ልይይት ትንተና (One way ANCOVA) ተተንትኗል። የተገኘው ውጤት እንዳመለከተውም በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ልዩነት ($F(1, 96)=18.004$, $p=.001$, $\eta^2=.159$) ተስተውሏል። በዚህም አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ መረዳትን ማሻሻሉ ተረጋግጧል። የተጽዕኖ መጠኑም መካከለኛ በመሆኑ አንብቦ የመረዳት ውጤትን ለማሻሻል እንደአንድ አማራጭ ሊያገለግል ይችላል። ውጤቱን በሌሎች ተማሪዎችና ቦታዎች ይበልጥ ለማጠቃለልም ለቀጣይ የጥናት ትኩረት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ቁልፍ ቃላት፤ አንብቦ መተረክ ብልሃት፣አንብቦ መረዳት

1 *Gondar College of Teacher Education, banchamlaktsegaye@gmail.com*
2 *PhD, Associate Professor, Bahir Dar University, marewalemu@gmail.com*
3 *PhD, Associate Professor, University of Gondar, agetesfa@gmail.com*

***This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.***
**DOI***:* https://dx.doi.org/10.4314/erjssh.v11i1.4

## መግቢያ

በግልጽ እንደሚታወቀው ማንበብ የግለሰቦችን ዕውቀት ያሳድጋል፤ የብስለት ደረጃና ባሕርይም ይገነባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማንበብ የሰዎች አስተሳሰብ የሰላ እንዲሆን ያደርጋል፤ ስለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ጉዳዮችም ግንዛቤ ያሰፋል፡፡ ማንበብ ለተማሪዎች መማር ብቻ ሳይሆን ለወደፊት የሕይወት ዘመናቸውም አስፈላጊ ነው (Grabe & Stoller, 2019)፡፡ በClark & Rumbold (2006) ጥናት እንደተረጋገጠውም ማንበብ በተማሪዎች የመማር ስኬት ላይ ተጽዕኖ አለው፡፡ በየቀኑ የሚያነቡ ተማሪዎች በቃላት ዕውቀታቸው፣ አንብቦ በመረዳት ችሎታቸውና በጠቅላላ ግንዛቤያቸው ልቀው ታይተዋል፡፡ ባህላቸውንም በተሻለ ደረጃ መረዳት ችለዋል፡፡ በመሆኑም የማንበብ ክሂል ከታችኛው የክፍል ደረጃ ጀምሮ መዳበር ይኖርበታል፡፡ Hausheer et al (2011) እንደገለጹትም የማንበብ ክሂል ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ራሳቸውን ከሚገነቡባቸው ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ ወሳኝ ነገር ነው፡፡

አንብቦ መረዳት ያነበቡትን የመገንዘብ፣ የመተርጎምና የመጠቀም ውስብስብ አእምሯዊ ችሎታ በመሆኑ፣ ሌሎች መሠረታዊ የማንበብ አላባውያንንም አቀናጅቶ መጠቀምን መጠየቁ፣ በንግግር ድምጽና በትዕምርተድምጻዊ ግንዛቤ፣ በአቀላጥፎ ማንበብና በቃላት ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በርካታ ተማሪዎች የክሂሉን መዳበር ለማሳካት ሲቸገሩ ይስተዋላል (Grabe, 2009, 2014)፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት በቋንቋ መማር ማስተማር መስክ የተለያዩ ንድፈሐሳቦች፣ ሞዴሎችና ብልሃቶች ሲፈልቁ ኖረዋል፤ አሁንም በመፍለቅ ላይ ናቸው፡፡ አንብቦ የመተረክ ብልሃትም አንብቦ ከመረዳት ጋራ የተያያዙ የተማሪዎችን ችግሮች ለመፍታት ከዳበሩ ብልሃቶች አንዱ ነው፡፡ ብልሃቱ ቀደምትነት ያለው ቢሆንም እስካሁንም አንብቦ መረዳትን በማስተማር ረገድ ሰፊ ትኩረት አግኝቷል (Goodman, 1982; Kesevan et al., 2023; Suriani & Yeni, 2023)፡፡

አንብቦ የመተረክ ብልሃት በተለያዩ ዘውጎች የቀረቡ ጽሑፎችን አንብቦ በአዲስ መንገድ በማደራጀት፣ በማዋቀር፣ በመገንባት ትርጉማቸውንና ጭብጣቸውን ሳይለቁ በራስ አባባል እንዲቀርቡ በማድረግ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት የሚያነቡትን ለመረዳት፣ ለማስታወስ፣ ከሌሎች ጋራ ለመወያየት ያግዛል፤ ብልሃቱ በጽሑፍ ውስጥ ውስን መረጃዎችን ነቅሶ ማውጣትን፣ አጭር መልስ መስጠትን፣ ዝግ ጥያቄዎችን መመለስን ከሚጠይቁ አቀራረቦች (piecemeal approaches) የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ብልሃቱ ስለተነበበው ታሪክ ሙሉ መረጃ የሚቀርብበትና ተማሪዎች የቀደመ ልምዳቸውን ተጠቅመው ሐሳቦችን እንደገና በማደራጀት እንዲገልጹ ዕድል ስለሚሰጥ ነው (Goodman,1982; John,2003; Morrow,1992; Praneetponkrang & Phaiboonnugulkij, 2014; Rhodes & Shanklin,1993; Suriani & Yeni, 2023; wittrock, 1981)፡፡

ይህ ብልሃት በአእምሯዊ የመማር ንድፈሐሳብ ውስጥ የሚገኘው አፍልቆታዊ የመማር ሞዴል መሠረት አለው፡፡ በዚህ ንድፈሐሳብ፣ መማር እውን የሚሆነው ተማሪዎች ንቁ ሆነው የሚያገኟቸውን አዳዲስ መረጃዎች ከቀደመዕውቀታቸው ጋራ ሲያገናኙ፣ በአዲስ መልክ ሲያደራጁና ከቀደመዕውቀታቸው ጋራ ሲያዋህዱ ነው፡፡ አንብቦ መተረክ ብልሃትም አእምሯዊ የሆኑና ከማንበብ ጋራ የተያያዙ ውስብስብ ተግባራትን የሚመለከት በመሆኑ አንብቦ ከመረዳት ጋራ ጥብቅ ቁርኝት አለው (Grabowski, 2004; Wittrock, 1974)፡፡

አንብቦ በመተረክ ብልሃት ቀደም ላሉት ዓመታት የማስታወስ ችሎታን ለማጥናት፣ ድምጽአልባ ፊልሞችን ተመልክተው ለመተረክና ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች ታሪካቸውን የሚናገሩባቸውን መንገዶች ለማጥናት በጥቅም ላይ ይውል እንደነበር በKalmbach (1986) የተጠቀሱት Bartlett (1932) እና O'Donnell, Griffin and Norris (1967) ይገልጻሉ፡ ፡ በጊዜ ሂደት ደግሞ ብልሃቱ በመደበኛ ትምህርትቤቶች በታችኞቹ የክፍል ደረጃዎች (ከ1-4ኛ ክፍሎች) የሚማሩ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን ጥቅም ላይ ዋለ፡፡ በአንደኛ ደረጃ መምህራን አመለካከትም፣ አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመመዘኛ ስልት እንጂ እንደማስተማሪያ ብልሃት መጠቀም ጊዜ የሚወስድ፣ አስቸጋሪና ትምህርታዊ ጠቀሜታ የሌለው ተደርጎም ይቆጠር ነበር (Marshall, 1983; Morrow, 1985; Taylor, 1982)፡፡

በወቅቱ ይካሄዱ የነበሩ ምርምሮች ትኩረትም አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ መረዳትን ለመመዘን በጥቅም ላይ ሲውል የሚኖረውን ጥራትና ደረጃ በማሻሻል ላይ ነበር (Brown & Cambourne, 1987; Gambrell et al., 1985 & Irwin & Mitchell, 1983)፡፡ አንብቦ በመተረክ ብልሃት አንብቦ መረዳትን በመመዘን ረገድም የተማሪዎች ዕድሜ፣ አስተዳደግ፣ ችሎታ፣ የአቀራረብ መንገድና የጽሑፉ ዓይነት የምዘና ሂደቱ ተግዳሮቶች መሆናቸው ታወቀ፡፡ Cao and Kim (2021) እንደገለጹት አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን ከሌሎች መመዘኛዎች የበለጠ ብቃትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ብልሃቱን ማንበብን ለማስተማሪያነት ማዋል የተሻለ እንደሆነ የሚመክሩ ሐሳቦች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ አንብቦ

የመተረክ ብልሃት አንብቦ መረዳትንም ሆነ ሌሎች የቋንቋ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችል ጠንካራ ብልሃት መሆኑን ጥናቶች ማመላከታቸውን ተከትሎም ብልሃቱ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር በሰፊው ጥቅም ላይ የመዋል ዕድሉን አገኘ (Goodman, 1982; Gillman & Carlile, 1997; Isbell, et al. 2004; Praneetponkrang & Phaiboonnugulkij, 2014; Regis-Onuoha, 2021; Samsudin & Sukrisno, 2016)። በተለይም በቅርብ ጊዜ ማንበብን ለማስተማር በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን የArahman et al (2024); Dalton,et al (2015); Samsudin and Sukrisno (2016); Suriani and Yeni (2023) ጥናቶች አመላካች ናቸው።

ይሁንእንጂ አንብቦ የመተረክ ብልሃት ማንበብን ለማስተማር ሲውል በአተገባበር ሂደት ሦስት መሠረታዊ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። አንደኛ፣ ተማሪዎች ለቃላት ዕውቀት ሰፊ ተጋልጦ ስለማይኖራቸው ሲሆን ብልሃቱን ተጠቅመው ያነበቡትን ለማቅረብ ሊቸገሩ ይችላሉ፤ ኹለተኛ፣ የተማሪዎች የቀደመዕውቀት ውስን መሆን በንባብ የተገኘውን አዲስ መረጃ ቀደምሲል ከነበረ መረጃ ጋራ የማስተሳሰር አቅም ሊያንሳቸው ይችላል፤ ሦስተኛ፣ አነስተኛ የቋንቋ ተጋልጦሽ ስለሚኖራቸው ሐሳባቸውን ለመግለጽ ሊቸገሩ ይችላሉ። በመሆኑም እነዚህ ውስንነቶች በብልሃቱ ውጤታማነት ላይ ተግዳሮት ሊሆኑ ይችላሉ (Risonar etal, 2021)። በተጨማሪም ብልሃቱ አንብቦ በመረዳት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ የሚወሰነው በጽሑፍ ዘውግና መጠን እንደሆነ McCormick and Cooper (1991) ጠቁመዋል።

የማንበብ ትምህርት በተለያዩ ብልሃቶች ቢታገዝም የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ግን አጥጋቢ እንዳልሆነ ያመላከቱ ጥናቶች አሉ (Atkins, 2013; Broer et al., 2002; Davis, 2010; Dymock, 2007; Nelson & Manset-Williamson, 2006 & Pressley, 2000)። የNational Reading Panel [NRP] (2000); Moyer and Galindo (2022) ጥናቶች እንደጠቆሙትም በአንደኛ ደረጃ የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች ለደረጃቸው የሚመጥን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የላቸውም። ይህም በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ምዘናዎች መሻሻል አላሳየም፤ ተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ የመቁረጫ ነጥብ ማሳካት አለመቻላቸውን ምዘናዎቹ አመላክተዋል። በቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችግርም እንደአካባቢና ማኅበራዊ ሳይንስና ሒሳብ ያሉ ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር እንቅፋት ይሆናል።

በአፍሪካ፣ በሰሜን አሜሪካና በእስያ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅም ጥናቶች ተካሂደዋል። ከምክንያቶች መካከልም Mohammed and Amponsah (2018); NRP (2000) እና Souriyavongsa et al (2013) እንደገለጹት ለማንበብ ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን፣ ተማሪዎች ሲያነቡ በጠቃሚ መረጃዎች ላይ ትኩረት አለማድረግ፣ በውጤታማ ብልሃቶች ተመሥርቶ አለማስተማር፤ የሚሉት ቀርበዋል። በBrooks and Dansereau (1983) ጥናትም፣ ለሐሳብ አደረጃጀት ትኩረት አለመስጠት እንደዋና ምክንያት ተጠቀሷል። በLindner (2008) እና Botha et al (2008) ጥናቶች ደግሞ ተማሪዎችን ለውጤታማ የማንበብ ብልሃቶች አለማጋለጥ፣ የተዛባ አመለካከትና ስለማንበብ ብልሃቶች ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆን፣ ከምንባቦች ዓይነትና ባሕርይ ጋራ የሚስማሙ የተለያዩ ብልሃቶችን አለመጠቀም በዋና ምክንያትነት ተጠቅሰዋል።

በኢትዮጵያ ደረጃም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው ጥናቶች ጠቁመዋል። ተማሪዎች አቀላጥፈው እንደማያነቡና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም በየክፍል ደረጃው ከሚጠበቀው በታች እንደሆነ የተከታታይ ምዘና ጥናቶች አሳይተዋል (EGRA, 2018; Tsehay, 2013)። ለዚህ የተማሪዎች ችግርም የተለያዩ የአተገባበር ምክንያቶች መኖራቸውን ጥናቶች ጠቁመዋል። ከምክንያቶቹ መካከልም ለምሳሌ፣ በተለያዩ የትምህርት ርከኖች የሚተገበረው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሂደት አንብቦ መረዳትን መሠረት ያላደረገ መሆኑን Abiy (2005) ጠቁመዋል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሚሰጠው የማንበብ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ፍላጎት የሚያሳድግ ሳይሆን ሰዋስዋዊ መዋቅሮችንና ሥነጽሑፍን በማስተማር እግረመንገዱን የሚከወን ተግባር መሆኑን Gessesse (1999) ገልጸዋል።

ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋራ በተደረገ ኢመደበኛ ውይይትም (የካቲት ወር 2015 ዓ.ም.)፣ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። በውይይቱ የተሳተፉ መምህራን እንደገለጹት፣ ተማሪዎች በማንበብ ተግባራት ላይ የነቃ ተሳትፎ አያሳዩም፤ ያነበቡትን በማደራጀት በራስ አባባል ለማቅረብ ይቸገራሉ፤ ለአመራማሪ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ አይሰጡም። የጥናቱ ዋና ትኩረቶች ባይሆኑም የአራተኛ ክፍል የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሐፎች ውስጥ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦችንና መልመጃዎችንም ለመቃኘት ተሞክሯል። በዚህም በክፍል ደረጃው የሥርዐተትምህርት መሣሪያዎች ውስጥ አንብቦ የመተረክ ብልሃት ትኩረት እንዳልተሰጠው ለመረዳት ተችሏል።

Kesevan et al. (2023) እንደገለጹት ግን አንብብ መተረክ ብልሃት በተለይም በትክክል ማንበብንና አንብቦ የመረዳት ችሎታዎችን የሚያሳድግ በመሆኑ ተማሪዎች በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይገባል። የዚህም ምክንያቱ አንብቦ ላለመረዳት ችግር ተተግባሪነትና ውጤታማነት ያለው ብልሃት እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ስለሆነም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት

ችሎታ በሚያጎለብቱ ብልሃቶች ላይ አጽንዖት በመስጠት ማንበብን ማስተማርና በዚሁ ላይ ምርምር ማካሄድ ያስፈልጋል (EGRA, 2010። ለዚህም አንብቦ ከመረዳት ጋራ ጥብቅ ትስስር ስላለው አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንድ አማራጭ ሊሆን ይችላል። አንብቦ በመተረክ ብልሃት ውስጥ የሚተገበሩት ወሳኝ ክንውኖች ስለተነበበው ጉዳይ በጥልቀት ማሰብን፣ ማብላላትን፣ ማደረጃትንና እንደገና ማዋቀርን የሚጠይቁ በመሆናቸው ብልሃቱ በጥልቀት የመረዳት ችሎታን ያጎለብታል (Johnston, 1983; Morrow, 1989 & Schisler et.al., 2010)።

ይሁንእንጂ፣ አንብቦ በመተረክ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጎልበትን በተመለከተ የተከናወኑ ምርምሮች በውጤቶቻቸው ወጥነት አይታይም። አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ በመረዳት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ያሳዩ ተመራማሪዎች (Gambrell et.al.,1991; Lin, 2010; Morrow, 1989 & Schisler, 2008) አሉ። ጥናቶቹም፣ ተማሪዎች አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን ሲማሩ ለሚያነቡት ጽሑፍ ሰፊ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎችን ይለያሉ፤ የጽሑፍን የሐሳብ ፍሰት በመረዳት ከምን በኋላ ምን እንደሚከተል ያውቃሉ፤ ስለጽሐፍ አወቃቀር የመገንዘብ አቅምን በማጎልበት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤ የሚሉ ድምዳሜዎች አሏቸው። በተቃራኒው አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ የRisonar, etal. (2021) ጥናት አረጋግጧል። በአተገባበር ሂደት ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች እንቅፋት እንደሚሆኑም የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። እነሱም አንደኛ፣ 91% የተማሪዎች የቃላት ዕውቀት ውስን መሆን፣ ኹለተኛ፣ 86% አንብቦ በመተረክ ሂደት የቀደመ ዕውቀት አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸው ዝቅተኛ መሆን ለትምህርቱ ሂደት እንቅፋት መሆንና ሦስተኛ፣ 86% ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ትምህርት ሂደት ውስጥ አነስተኛ የሆነ የቋንቋ ተጋልጦሽ መኖር ብልሃቱን በትክክል ለመተግበር እንቅፋት መሆናቸው ተጠቀስሷል።

በተጨማሪም፣ McNeil et al. (2001) እንዲሁም Yu-Ling and Linan-Thompson (2022) አንብቦ የመተረክ ብልሃት በተለይም የመማር እክል ያለባቸውን ተማሪዎች አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መለየት እንደሚያስችል ጠቁመዋል፡ ፡ ነገርግን ጽሑፍ አንብቦ ለመተረክ ዝርዝር መረጃዎችን ማስታወስ፣ ትርጉም ባለው መንገድ ማደራጀት፣ በመረጃዎች መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመርና ማጠቃለል በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ ጥገኛ ስለሚሆኑ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር አመቺ እንዳልሆነም ጠቁመዋል።

ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንጻር አንብቦ የመተረክ ብልሃት በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ስላለው አስተዋፆ በተመለከተ ተደራሽ ከሆኑት ምንጮች በኢትዮጵያ ጥናቶችን ማግኘት አልተቻለም። ይህም ብልሃቱን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ማስተማር ዐውድ በመተግበር ውጤታማነቱን መፈተሽ ምክንያታዊ ያደርገዋል። በተጨማሪም ከላይ የተቃኙት ምርምራዊና ተመክሯዊ ክፍተቶችም ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ሆነዋል።
በዚህም መሠረት የጥናቱ መላምት የሚከተለው ነው፤

መ$_{አል.}$ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የለውም።
መ$_{አማ.}$ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ አለው።

## የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመርመር ነው። ይህንን ዓላማ ከዳር ለማድረስም ጥናቱ ቅድመትምህርትና ድኅረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን ፍትነትመሰል የጥናት ንድፍን (Quasi-Experimental pretest posttest control group design) ተከትሏል። ንድፉ የተመረጠበት ዋና ምክንያትም የጥናቱን ተሳታፊዎች በሚማሩበት ክፍል እንዳሉ (ቡድኑ በሙሉ) በተፈጥሯዊ መገኛቸው ለማጥናት ስለሚያስችል ነው።

## ተሳታፊዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች በጎንደር ከተማ በመሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት በ2015 ዓ.ም. በመማር ላይ ከነበሩ ከአራት የአራተኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል በቀላል የዕጣ ንሞና የተመረጡ ኹለት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች ከተመረጡት ኹለት መማሪያ ክፍሎች በእያንዳንዱ 49 በአጠቃላይ 98 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል። የመሠረት አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት ጥናቱ እንዲካሄድበት የተመረጠው ከትምህርትቤቱ አስተዳደር ፈቃድና ይሁንታ ስለተገኘ ነው። አራተኛ ክፍልም የተመረጠው በምክንያት ንሞና (purposive sampling) ነው። የዚህም

ምክንያቱ ተማሪዎች ለማንበብ ከመማር ወደለመማር ማንበብ የሚሸጋገሩበት (Ehri, 2005; NRP, 2000)፣ በሀገራቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የትምህርት ርከኑን የብቃት ደረጃ ለማረጋገጥ የብቃት መለኪያ ፈተና የሚሰጥበትና አንብቦ የመረዳት ችግር በስፋት ከታየባቸው የክፍል ደረጃዎችም አንዱ በመሆኑ ነው (Abiy, 2005; EGRA, 2018; Gessesse, 1999; Tsehay, 2013)። አንብቦ የመተረክ ብልሃት በታችኛው የክፍል ደረጃ ተተግብሮ ውጤታማ እንደሆነ ያመለካቱ ጥናቶች መኖራቸውም ሌላው ምክንያት ነው (Ebaugh, 2013; Gambrell et al, 1991)።
የክፍል ደረጃው ተማሪዎች የዕድሜ፣ የፆታና የችሎታ ተመጣጣኝነታቸውን ለማወቅ በቅድመትምህርት ፈተናው መረጃ አማካይነት ፍተሻ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የኹለቱ ቡድኖች ተማሪዎች የዕድሜ ተመጣጣኝነት ደረጃ በነጻና ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ $t(96)= .131$, $p= .896$ ሆኗል። የኹለቱ ቡድኖች ተማሪዎች የፆታ ተመጣጣኝነትም በካይ ካሬ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት $x^2(1) = .001$, $p= 1.00$ ሆኗል። ከችሎታ አንጻር ደግሞ ተማሪዎች በቅድመትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያስመዘገቡት ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት $t(96)= .347$, $p=729$ ሆኗል። በሁሉም ረገድ ተሳታፊዎች በፆታ፣ በዕድሜና በችሎታ የጎላ ልዩነት እንደሌላቸው ተረጋግጧል። ይህም ፆታና ዕድሜ አበር ሳይሆኑ፣ ችሎታ (ቅድመፈተናው) ግን የፈተና ተጽዕኖን ለመቆጣጠር አበር ሆኖ መተንተን እንዳለበት አመላካች ሆኗል።

## የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ

የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው አንብቦ በመረዳት ችሎታ ፈተና ሲሆን የዚህም ዋና ዓላማ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን ተማሪዎች በቅድመትምህርትና በድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ነው። ፈተናው የተዘጋጀው ከአንድ ምንባብ ሲሆን ይህም ከብርሃኑና ሌሎች (2016) የተወሰደ ነው። የዚህም ምክንያቱ በክፍል ደረጃው በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግሞ ለክፍል ደረጃው በይዘትም በቅርጽም የሚመጥን ሆኖ ስለተገኘ ነው።

ፈተናውን ለማዘጋጀትም አስቀድሞ በሥርዐተትምህርቱ መሣሪያዎች መነሻነት የፈተና መወሰኛ ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡ ፡ በዚህም መሠረት 26 ባለመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በፈተናውም በክፍል ደረጃው ሥርዐተትምህርት መሠረት ጥያቄዎቹ ቀጥተኛ፣ አንድምታዊና ሂሳዊ አንብቦ የመረዳት ንኡስ ክሂሎች እንዲካተቱ ተደርጓል።

የፈተናው አስተማማኝነትና ትክክለኛነትም በቅድመና ድኅረትምህርት ተፈትሿል። በዚህም መሠረት በክሮምባኽ አልፋ የተገኘው የአስተማማኝነት ውጤት በቅደምተከተል = .717 እና □= .787 ሆኗል። ውጤቱም ተቀባይነት ያለው ነው፡ ፡ ትክክለኛነቱንም በተመለከተ ፈተናው ለስድስት የአንደኛ ደረጃ፣ የኮሌጅና የዩኒቨርሲቲ መምህራን ተሰጥቶ እያንዳንዱ ጥያቄ አንብቦ መረዳትን ለመለካት ጠቃሚ ነው (1) ወይም ጠቃሚ አይደለም (0)፤ በሚሉ አማራጮች እንዲገመግሙት ተደርጎ መረጃው በLawshe (1975) ቀመር ተሰልቶ ውጤቱ □= .99 ሆኗል። ይህም በአጠቃላይ ፈተናው በቅርጽ፣ በይዘትና በሚለካው ባሕርይ ትክክለኛና ተገቢ መሆኑን አመላክቷል።

## ማስተማሪያ መሣሪያ

በዚህ ጥናት የሙከራውም ሆነ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የተማሩት በ2015 ዓ.ም በሥራ ላይ በዋለው የተማሪ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ ምንባቦች ነው። ለዚህም ምክንያቱ አንብቦ ከመተረክ ብልሃት ውጭ ኹለቱ ቡድኖች በተመሳሳይ የትምህርት መሣሪያዎች እንዲማሩ ስለተፈለገ ነው። በዚህም መሠረት ለሙከራ ቡድኑ ማስተማሪያ Lin (2010) ያሻሻሉት መር-የትረካ አቀራረብ ቀደምሲል ሌሎች ተመራማሪዎችም (Benson & Cummins, 2000; Bernhardt, 1991; Koskinen et al. 1988) የተጠቀሙበት አንብቦ የመተረክ ሞዴል ተግባራዊ ሆኗል። በዓይነት ደረጃም ከቃላዊው፣ ጽሑፋዊውና ሥዕላዊው ብልሃት (Han, 2005) ቃላዊው ተተግብሯል። ብልሃቱ ቀጥተኛ ገለጻ፣ አርኣያ ሆኖ ማሳየት፣ በትብብርና በግል መማር፤ በሚሉ አራት ደረጃዎች እንዲቀርብ ሆኗል። አራቱ ደረጃዎች በቅደምተከተል ለኹለት፣ ለአራት፣ ለአራትና ለስድስት መደበኛ ክፍለጊዜያት (አንድ ክፍለጊዜ 40 ደቂቃ) ተከፋፍለው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለስምንት ሳምንት፣ (በሳምንት ለኹለት ክፍለጊዜ)፣ በአጠቃላይም ለ16 ክፍለጊዜ እንዲለማመዱባቸው ተደርጓል።

## የአጠናን ሂደት

ጥናቱን ለማካሄድ በመጀመሪያ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል በተጻፈ የትብብር ደብዳቤ አማካይነት የትምህርትቤቱ አስተዳደር ፈቃድ ተጠይቋል። የአስተዳደሩ ይሁንታ ከተገኘ በኋላም ለክፍል ደረጃው መምህርትና ለተማሪዎች ስለጥናቱ ዓላማ ግንዛቤ ተፈጥሯል። በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ በጥናቱ ለመሳተፍ የይሁንታ ስምምነት ቅጽ ወላጆቻቸውን አስፈርመው እንዲመጡ ተደርጓል።

ለተግባሪ መምህሯም ስለጥናቱ አተገባበር ሂደት በተዘጋጀው የብልሃት ማስተማሪያ አማካይነት ስለአንብቦ መተረክ ብልሃት ምንነት፣ የአተገባበር ደረጃዎች፣ ስለብልሃቱ መርሆዎች፣ ስለተማሪዎች ተግባራትና ኃላፊነቶች ለኹለት ቀን የአራት፣ የአራት ሰዓት በድምሩ የስምንት ሰዓት ስልጠና ተሰጥቷል። ይህም እንደተጠናቀቀ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ተማሪዎች የቅድመትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተፈትነዋል። የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አንብቦ በመተረክ ብልሃት የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ በመደበኛው ሥርዐተትምህርት መሠረት ለስምንት ሳምንታት (ለ16 ክፍለጊዜ) የማንበብ ትምህርት ተምረዋል።

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የማንበብ ትምህርት ስለብልሃቱ በቀጥታ በማብራራት፣ አርኣያ ሆኖ በማሳየት፣ በጋራና ራሥን ችሎ በመሥራት የተደራጀ ነው፤ የዚህም ምክንያቱ በሂደቱ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የመሥራት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ታስቦ ነው። የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ተማሪዎች የማንበብ ትምህርት ትግበራ ሂደትም በመምህርና ተማሪ የጽብረቃ ቅጽ አማካይነት ክትትል ተደርጎበታል። ለመረጃው ውስጣዊ ትክክለኛነት ሲባልም የመለማመጃ ቅጾችና በግድግዳ ላይ የሚለጠፉ አንብቦ የመተረክ ብልሃት መመሪያ ሽራ በየክፍለጊዜው መጨረሻ እንዲሰበሰቡ ተደርጓል፡ ፡ ከተመራማሪዎቹም አንዷ በአራቱ የትግበራ ደረጃዎች አንድ፣ አንድ ጊዜ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘት ክትትል አድርጋለች። በቁጥጥር ቡድኑ መማሪያ ክፍሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ምልከታ አድርጋለች፡ ፡ በመጨረሻም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ሁሉም ተማሪዎች የድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተፈትነዋል።

የሙከራ ትምህርቱ ከተጠናቀቀና የጥናቱ አዎንታዊ ውጤት ከታወቀ በኋላ ለቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች አንብቦ በመተረክ ብልሃት አማካይነት የማካካሻ የማንበብ ትምህርት ተሰጥቷል። ትምህርቱም በመደበኛው አንድ ክፍለጊዜ ስለብልሃቱ ቀጥተኛ ገለጻ በማድረግ ቀሪዎቹን የብልሃት ትምህርት ሂደቶች በአራት ምንባቦች (ዶሮ ነጋዴው፣ አተርፍባይ አጉዳይ፣ ስኬት በጥረትና ጋዜጠኛዋ) በተግባሪ መምህርቷ ቀርቧል።

## የመረጃ አተናተን

የጥናቱ መረጃዎች በአግባቡ ከተደራጁና ከተጣሩ በኋላ በspss v20፣ በባለአንድ አቅጣጫ አበር የልይይት ትንተና (One way ANCOVA) ተተንትነዋል። ይህ ትንተና የተመረጠበት ምክንያትም የቅድመትምህርት ፈተናውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር ነው። ቅድመትምህርት ውጤቱ በድኅረትምህርት ውጤቱ ላይ ያሳየው የትንበያ ድርሻ ($R^{2}$=.201/20%, p=.001) ሲሆን፣ የልይይት (variance) ድርሻው ደግሞ .799 ስለሆነና የቅድመትምህርት ፈተናው በቡድኖች መካከል ልዩነት ፈጣሪ መሆኑን ስላመለከተ ቅድመትምህርት ውጤቱን አበር አድርጎ መቆጣጠር አስፈላጊ ነበር። ለዚህም የአበር ተላውጦውን መረጃ ከሙከራ በፊት መሰብሰብ፣ የውጤት ስርጭት ወጥነት መፈተሽ (normality)፣ የልይይት ስሕተት አንድነት (homoginity)፣ ቅድመና ድኅረትምህርት ፈተናዎች ቀጥተኛ ግንኙነት (linearity) እና የአበር ተላውጦውን አስተማማኝነት ማረጋገጥ በቅድመሁኔታነት ተፈትሸዋል።

ከውጤት ስርጭት ወጥነት አንጻር በቅድመትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ በተከታታይ የተገኘው የ"ሻፒሮ ዊልክስ" ውጤት .129 እና .069 ሆኗል። በድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናው ደግሞ በሙከራና በቁጥጥሩ የተገኘው ውጤት በተከታታይ .255 እና .126 ሆኗል። የመረጃው የሾልነት (skewnes) እና የጠፍጣፋነት (kurtosis) ደረጃ የዜድ ዋጋው ሲታይም በ-1.96 እና በ1.96 መካከል ሆኗል። ከልይይት ስሕተት አንድነት አንጻር ደግሞ መረጃው ተፈትሾ የተገኘው የለቨን ውጤት በቅድመትምህርት በኹለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘው ውጤት $F$(1, 96) =.00, $p$= .999 ሲሆን፣ በድኅረትምህርት $F$(1, 96) =.728, $p$= .396 ሆኗል። ይህም በኹለቱ ቡድኖች መካከል የልይይት ስሕተት ልዩነት አለመኖሩን አመላክቷል። ከመረጃዎች ቀጥተኛ ግንኙነት አንጻርም የቅድመትምህርትና የድኅረትምህርት ውጤቶች ቀጥተኛ ግንኙነት ተሰልተው የተገኘው የቀጥተኛነት ውጤት (Linearity) $p$=.001 ሲሆን፣ ከቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ርቀት ደግሞ (Deviation from Linearity) $p$=.463 ሆኗል። በተጨማሪም በቅድመና በድኅረትምህርት ፈተና ውጤቶች መካከል ያለው ዝምድና ተሰልቶ የተገኘው ውጤት $r$=.490, $p$=.001 ሆኗል፡ ፡ ውጤቱ በብትን ግራፍ ሲታይም ትይዩነትን አሳይቷል።

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

የጥናቱ አማራጭ መላምት "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ አለው።" የሚል ነበር። ይህንንም ለመፈተሽ መረጃው በባለአንድ አቅጣጫ አበር ልይይት ትንተና (One way ANCOVA) ተተንትኗል። ከጥናቱ መላምት አንጻር የገኘው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ $F$ (1, 96)=

18.004, $p < .001$, $\eta^2 = .159$ መኖሩን አሳይቷል፡፡ ውጤቱም በቡድኖች መካከል የጉልህነት ደረጃው መካከለኛ የሆነ ልዩነት መኖሩን አመላካች ነው፡፡ በዚህም መሠረት አልቦ መላምቱ ውድቅ ሆኖ አማራጭ መላምቱ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ከላይ በውጤት ትንተናው እንደተገለጸው አንብቦ መተረክ ብልሃት ከመደበኛው ሥርዐተትምህርት አቀራረብ በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንደሚያሳድግ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ውጤት ከKesevan et al., (2023); Morrow (1986); Regis-Onuoha (2021) እና Suriani & Yeni (2023) ጥናቶች ውጤቶች ጋራ ተደጋጋፊ ሆኗል፡፡ በእነዚህ በሁሉም ጥናቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማሳደግ ረገድ አንብቦ የመተረክ ብልሃት ውጤታማነት ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤት ከGambrell et al, (2016)፣ ከLabibah, (2021)፣ ከHan, (2005)፣ ከRudiawan and Jupri, (2020) እና ከ Trisnawati, (2017) ጥናቶች ውጤቶች ጋራ ተደጋጋፊ ሆኗል፡፡ ከአራተኛ እስከ11ኛ ባሉ የክፍል ደረጃዎች የተካሄዱት እነዚህ ሁሉም ጥናቶች አንብቦ መተረክ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳሻሻለ አመላክተዋል፡፡ እንዲሁም የዚህ ጥናት ውጤት በተመሳሳይ ሁኔታ በአፍመፍቻ ቋንቋ ላይ ካተኮረው ከእነRudiawan and Jupri (2020) ጥናትና በኹለተኛ ቋንቋ ላይ ትኩረት ካደረገው ከTrisnawati (2017) ጥናት ውጤት ጋራም ተደጋጋፊነት አሳይቷል፡፡

አንብቦ በመተረክ ብልሃት ትግበራ አማካይነት የተገኘው የዚህ ጥናት ውጤት ቃላዊ፣ ጽሑፋዊና ሥዕላዊ የትረካ ብልሃቶችን አወዳዳሪ መንስዔያዊ በሆነ ንድፍ ተተግብሮ (Han, 2005)፣ እንዲሁም ቃላዊውን አንብቦ መተረክ ከመደበኛው ሥርዐተትምህርት አቀራረብ ጋራ በማወዳደር (Gambrell et al, 2016) ላይ አተኩረው የብልሃቱን ውጤታማነት ካረጋገጡት ጥናቶች ውጤት ጋራ ተደጋጋፊ ሆኗል፡፡ በጥናቶቹ በቃላዊውና በጽሑፋዊው አንብቦ መተረክ ብልሃቶች ምክንያት በተወዳዳሪ ቡድን ተማሪዎች መካከል አንብቦ በመረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት አልታየም፤ ኹለቱም ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን በማሳደግ ረገድ ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋገጠው የEbaugh, (2013) ጥናት ውጤትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለብልሃቱ ውጤታማነት በአስረጂነት የተጠቀሱት ጥናቶች የተለያዩ ንድፎችንና የምርምር ዘዴዎችን የተከተሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ Rudiawan and Jupri (2020) እና Gambrell et al (2016) የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ንድፍን፣ Trisnawati (2017) ደግሞ በአንድ ቡድን የቅድመ-ድኅረትምህርት ፈተና ፍትንትመሰል ንድፍን ተከትለዋል፡፡ የአጠናን ዘዴን በተመለከተ የLabibah (2021) ዓይነታዊ ሲሆን፣ የMorrow (1986) እና የKelly (1998) መጠናዊ ናቸው፡ ፡ የእነዚህ ጥናቶች ንድፍና የአጠናን ዘዴ ቢለያይም ግን ውጤቶቻቸው ተመሳሳይ ናቸው፤ የሁሉም ጥናቶች ውጤቶች ማንበብን በማስተማር ረገድ አንብቦ የመተረክ ብልሃትን ውጤታማነት ያመላከቱ ናቸው፡፡

በአንጻሩ የዚህ ጥናት ውጤት በስድስተኛ ክፍል (Risonar et al, 2021)፣ በአራተኛ ክፍል (D'Alessio, 1996) እና በመዋዕለ ሕጻናት ደረጃ (Morrow, 1985) ካተኮሩ ጥናቶች ውጤቶች ጋራ የሚደጋገፍ አልሆነም፡፡ የዚህም ምክንያቱ ምናልባት በጥናቶቹ ከተጠቀሱት ውስንነቶች ጋራ የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ በRisonar et al ጥናት አንብቦ መተረክ ብልሃት ተግባራዊ ሆኖ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ልዩነት አልታየም፡፡ ለዚህም የተማሪዎች ጠቅላላ ዕውቀት አለመዳበር፣ የቀደመዕውቀት አለመኖር፣ የቃላት ዕውቀት እጥረትና ለእንግሊዝኛ ቋንቋ በስፋት አለመጋለጥ በውስንነት ተጠቅሰዋል፡፡ በD'Alessio ጥናት ደግሞ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ልዩነት ላለመታየቱ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች በጥያቄና መልስ ስልት፣ በተራኪ ጽሑፍ ጥያቄዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው መለማመዳቸው፣ በአንጻሩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለዚህ ዓይነት ተመክሮ አለመጋለጣቸው በውስንነት ቀርበዋል፡፡ እንዲሁም አንብቦ የመተረክ ብልሃት የልምምድ ጊዜ ማነስና ታሪኮችም. ስድስት ብቻ መሆናቸውም በተጨማሪ ውስንነት ተጠቅሰዋል፡፡ በMorrow ጥናት ደግሞ ተደጋጋሚ ልምምድ አንብቦ የመተረክ ብልሃትን ውጤታማ ሊያደርገው እንደሚችል ታሳቢ ቢደረግም በጥናቱ ሂደት ግን ተማሪዎች ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን እየዘለሉ ሲያጠቃልሉ እንደነበር፣ ታሪኩን አለመጨረስ እንደተስተዋለባቸውና ሲጀምሩ መደናገር ይታይባቸው እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም መር ልምምድ ያስፈልግ እንደነበር ተጠቁሟል፡፡

ይህም ጥናት ቢሆን ከምንም ዓይነት ውስንነቶች ነጻ ነው፤ ማለት አይቻልም፡፡ ጥናቱ በአንድ ከተማ፣ በአንድ ትምህርትቤት በኹለት ክፍል ተማሪዎች ብቻ በስምንት ሳምንት ልምምድ የተካሄደ በመሆኑ ውጤቱን በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ለሌሎች ሰፊ አካባቢዎች ለማጠቃለል የሚቻል አይሆንም፡፡ ለዚህም ተመሳሳይ ጥናት ረዘም ላለ ጊዜ በብዙ ናሙና ቁጥር ቢካሄድ አንብቦ ስለመተረክ ብልሃት ውጤታማነት የተሟላ ግንዛቤ ሊገኝ ይችላል፡፡

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አንብቦ በመተረክ ብልሃት ማንበብን መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመር ሲሆን፣ የጥናቱ ንድፍም ፍትነትመሰል ቅድመና ድኅረትምህርት ባለቁጥጥር ቡድን ነበር፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በጎንደር ከተማ በመሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት በ2015 ዓ.ም. በመማር ላይ ከነበሩ ከአራት የአራተኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል በቀላል የዕጣ ንሞና የተመረጡ ኹለት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡ ፡ በእጣ በተመረጡ ኹለት የመማሪያ ክፍሎች በእያንዳንዱ 49 በአጠቃላይ 98 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ የጥናቱ መረጃም አንብቦ በመረዳት ፈተና የተሰበሰበ ሲሆን፣ አስተማማኝነቱና ትክክለኛነቱም ተረጋግጧል፡፡ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ፈተና የተገኘው መረጃም በባለአንድ አቅጣጫ አበር ልይይት (One way ANCOVA) ስልት ተተንትኗል፡፡ ውጤቱ እንዳመለከተውም አንብቦ የመተረክ ብልሃት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ የተጽዕኖ መጠኑ መካከለኛ የሆነ ($\eta^2$ =.159) አዎንታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ አንብቦ መተረክ ብልሃት አንድ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

## አስተያየት

በዚህ ጥናት አንብቦ የመተረክ ብልሃት በአራተኛ ክፍል ደረጃ ተተግብሮ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ አዎንታዊ አስተዋፆ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በተለይም ጥናቱ በተተገበረበት አካባቢ የአራተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ብልሃቱን ጥናቱ በተተገበረበት መልክ ማንበብን በማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ ቢተገብሩት ውጤታማ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

በተጨማሪም በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው በአንድ ትምህርትቤትና አንድ የክፍል ደረጃ ስለሆነ አንብቦ ስለመተረክ ብልሃት የተሟላ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲቻል ተመሳሳይ ጥናት በብዙ የናሙና ቁጥር በሰፊ አካባቢዎች ለተራዘመ ጊዜ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## ምስጋና

ለዚህ ጥናት ዳር መድረስ በ2015 ዓ.ም. በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሆኑትን የመሠረት አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ4ኛ 1 እና 3 ክፍሎች ተማሪዎችና ወላጆች፣ የክፍሎቹን መምህርት መሰሉ ሰጥአርገው፣ የጥናቱን ጽሑፍ በማረም ገንቢ አስተያየት የሰጡትን አንዳርጋቸው መንገሻን (አማርኛ በማስተማር ፒኤችዲ ተማሪ)ና በመረጃ ትንተናው ላይ ሙያዊ እገዛ ያደረጉትን ዶር. አራጋው ሺባባውን፣ ጥናቱ ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልንን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

## References

ብርሃኑ ቦጋለና ሌሎች። (2016)። እኔና ወንድሜ። አራተኛ ክፍል ተመጣጣኝ ንባብ፣ መጽሐፍ 3። ተሸሽሎ የተወሰደ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2013)። የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተትምህርት የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች። ባሕር ዳር።

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርትቢሮና የምሁራን መማክርት ጉባዔ፡ ፡ (2015 ዓ.ም)። አማርኛ፤ የተማሪመጽሐፍ፣ 4ኛክፍል።

Abiy Yigzaw. (2005) .*Effects of teacher mediation on student conceptions and approaches to reading*. [Unpublished manuscript]. Addis Ababa University; Addis Ababa.

Arahman, F. R., Kamil, A. B., & Sumartra, S. (2024). Students' Emotional Enggagement in Reading Comprehension Through Read, Cover, Remember and Retell (RCRR) Strategy. *EDULIA: English Education, Linguistic and Art Journal*, *4*(2), 91-97.

Atkins, J. G. (2013). *The effect of explicit teaching of comprehension strategies on reading comprehension in elementary school* (Doctorial dissertation). Graduate School of Arts and Sciences, Columbia University.

Bernhardt, E. B. (1991). Reading development in a second language: Theoretical, empirical and classroom perspectives. Norwood, NJ: Ablex.

Benson, V., & Cummins, C. (2000). The power of retelling: Developmental steps for building comprehension. WA: The Wright Group.

Botha, D., Bizos, N., Gains, P., Moris, D., Place, J., & Puwani, H. (2008). National reading strategy. *Department of Education, Republic of South Africa, Pretoria.*

Broer, N. A., Aarnoutse, C. A. J., Kieviet, F. K., & van Leeuwe, J. F. J. (2002). The effect of instructing the structural aspect of texts. *Educational Studies*,28 (3), 213-238. Retrieved doi.org/10.1080/0305569022000003681l5. Accessed: 07/11/2014 06:46

Brown, H.& Cambourne, B. (1987). *Read and retell.* Portsmouth, NH: Heinemann Educational Books..

Brooks, L.W. & Dansereau, D. F. (1983). Effect of structural schema training and text organization on expository prose processing. *Journal of Educational*

*Psychology*,75 (6),811-82

Clark, C., & Rumbold, K. (2006). Reading for Pleasure: A Research Overview. *National Literacy Trust.*

Cao, Y., & Kim, Y. S. G. (2021). Is retell a valid measure of reading comprehension?. *Educational research review*, *32*, 100375.

D'Alessio,J.A.(1996). Retelling in the Improvement ofReading Comprehension Scores of Urban, Lower Socio-EconomicFourth Graders. s department of educationcr., n.i1,a. nna. resealch and irnpfoyenvni ed cational resourcesinformationcenter (eric.).

Dalton, B., Robinson, K. H., Lovvorn, J. F., Smith, B. E., Alvey, T., Mo, E., ... & Proctor, C. P. (2015). Fifth-grade students' digital retellings and the Common Core: Modal use and design intentionality. *The Elementary School Journal*, *115*(4), 548-569.

Davis, D. S. (2010). *A meta-analysis of comprehension strategy instruction for upper elementary and middle school students.*[ Unpublished Doctorial dissertation]. Graduate School of Vanderbilt University, Nashville, Tennessee.

Dymock, S. (2007). Comprehension strategy instruction: Teaching narrative text structure awareness. *The Reading Teacher, 61*(2), 161-167. Retrieved from http://www. jstor.org/ stable/20204567. Accessed: 07/11/2014 03:47.

Early Grade Reading Assessment. (2010). *Ethiopian early grade reading assessment: Data analytic report: Language & early learning.* Addis Ababa (USAID/Ethiopia).

Early Grade Reading Assessment. (2018). *Early Grade Reading Assessment Expansion: Ethiopia- Data Analytic Report: Language and Early Learning*. Addis Ababa, Ethiopia.

Ebaugh, K.(2013).The Effect of oral and written retell strategies for Informational Text on Reading Comprehension Performance of Fifth Grade Students. *Education -- Research papers* Goucher College.doi:10.13016/M2R731

Ehri, L. C. (2005). Learning to read words: Theory, findings, and issues. *Scientific Studies of reading*, *9*(2), 167-188.

Gambrell et al. (2016). Reading Comprehension and Recall of 'Text Information. *Taylor & Francis Group.* http://www.tandfonline.com/loi/vjer20

Gambrell, L. B., Kapinus, B., & Koskinen, P.S. (1991). Retelling and the reading comprehension of proficient and less-proficient readers. *The Journal of Educational Research, 84,* 356-362.

Gambrell, L.B., Pfeiffer, W.R., & Wilson, R.M. (1985). The effects of retelling upon reading comprehension and recall of text information. *Journal of Educational Research.78*(4).

Gessesse Tadesse. (1999).The effect of a process approach to teaching reading on first year students at Kotebe college of teacher education. [Unpublished manuscript]. Addis Ababa University; Addis Ababa.

Gillman, R. B., & Carlile, R. M. (1997). Oral reading and story retelling of students with specific language impairment. Language, Speech, and Hearting Services in Schools, 28, 30 – 42

Goodman, Y. (1982).Retellings of literature and the comprehension process. *Theory Into Practice 21* (4), p. 301-308.

Grabe, W. (2014). Key issues in L2 reading development. In *Proceedings of the 4th CELC Symposium for English Language Teachers-Selected Papers* (pp. 8-18).

Grabe, W. (2009). Reading in a second language: *Moving from theory to practice*. Ernst Klett Sprachen.

Grabe, W., & Stoller, F. L. (2019). *Teaching and researching reading*. Routledge.

Grabowski, B. L. (2004). Generative learning contributions to the design of instruction and learning. In D. H. Jonassen (Ed.*), Handbook of research on educational communications and technology* (2nd ed., pp. 719– 743). Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Han, J. (2005). Retelling as an effective reading comprehension strategy for young ESL learners.[Iowa State University, Master thesis].

Hausheer, R., Hansen, A., & Doumas, D. M. (2011). Improving reading fluency and comprehension among elementary students: Evaluation of a school remedial reading program. *Journal of School Counseling, 9*(9), n9.

Irwin, & Judy Nichols Mitchell .(1983). A Procedure for Assessing the Richness of Retellings. *Journal of Reading, Vol. 26,* No. 5 Wiley on behalf of the International Reading Association Stable URL: http://www.jstor.org/stable/4003449.

Isbell, R. T. (2002). Telling and retelling stories: Learning language and literacy. *Young Children 57* (2): 26–30.

John, S. F., Lui, M., & Tannock, R. (2003). Children's story retelling and comprehension using a new narrative resource. *Canadian Journal of School Psychology, 18*(1-2), 91-113.

Johnston, P.H. (1983). Reading comprehension assessment: A cognitive basis. Newark, DE: *International Reading Association*.

Kalmbach, J.R. (1986). Evaluating Informal Methods for the Assessment of Retellings. *Journal of Reading, 30.* (2). 119-27.

Kelly,K. (1998). The Effects of Usinga Combination of Story Frames and RetellingStrategies with Learning Disabled Studentsto Build Their ComprehensionAbility. *DOCUMENT RESUME.*[ Kean University, Master thesis].

Kesevan, H. V., Ridzwan, N. D. R., Gopal, R., & Swaran Singh, C. K. (2023). Written Retelling Strategy in Improving Reading Skill among ESL Students in Malaysia. *Education Research International, 2023*.

Koskinen, P. S., Gambrell, L. B., Kapinus, B. A., & Heathington, B. S. (1988). Retelling: A strategy for enhancing students' reading comprehension. *The Reading Teacher, 41*(49), 892-896. Retrieved on June 15, 2014 from http://www.jstor.org/stable/20199962

Labibah, H,F.(2021) The use of retelling story narrative text in reading comprehension in the rural area. *UNNES-TEFLIN National Seminar* 4(1), 2021 p-ISSN 2580-7501 e-ISSN 2580-751X.

Lawshe, C. (1975). A quantitative approach to content validity. Personnel Psychology, 28, 563-575.

Lindner, A. B. (2008). *INFORMATIONAL TEXT: READING STRATEGIES INSTRUCTION AND RELATIONSHIP TOWARD SCIENCE* (Doctoral dissertation, Sierra Nevada College).

Lin. L (2010). The Impact of the Retelling Technique on Chinese Students'English Reading Comprehension; *The Asian EFL Journal*. Volume *12*, Issue( 2)163-191

Marshall, N. (1983).Using Story Grammar to Assess Reading Comprehension.*The Reading Teacher, 37*, 161-65.

McCormick, S., & Cooper, J. O. (1991). Can SQ3R Facilitate Secondary Learning Disabled Students'literal Comprehension Of Expository Test? Three Experiments. *Reading Psychology: An International Quarterly*, *12*(3), 239-271.

McNeil, M. R., Doyle, P. J., Fossett, T. R., Park, G. H., & Goda, A. J. (2001). Reliability and concurrent validity of the information unit scoring metric for the story retelling procedure. *Aphasiology*, *15*(10-11), 991-1006.

Mohammed, I., & Amponsah, O. (2018). Predominant Factors Contributing to Low Reading Abilities of Pupils at Elsie Lund Basic School in the Tamale Metropolis, Ghana. *African Educational Research Journal*, *6*(4), 273-278.

Morrow, L. M. (1986). Effects of Structural Guidance in Story Retelling on Children's Dictation of Original Stories .*Journal of Reading Behavior,18*(2),135-152.

Morrow, L. M., Sisco, L. J., & Smith, J. K. (1992). The effect of mediated story retelling on listening comprehension, story structures, and oral language development in children with learning disabilities. In C. K. Kinzer, D. J. Leu, & J. A. Peter (Eds.), Literacy research, *theory, and practice*: Views from many perspectives .

Morrow, L.M (1985 a) . Reading and Retelling Stories: Strategies for Emergent Readers. *The Reading Teacher, 38,* 70-77.

Morrow, L.M. (1985b). Retelling stories: A strategy for improving young children's comprehension, concept of story structure, and oral language complexity.*The Elementary School Journal, 85*(5), 646-661.

Morrow, L.M. (1989). Using story retelling to develop comprehension. In K.D. Muth (Ed.),

Children's comprehension of text: *Research into practice* (pp. 37–58). Newark, DE:International Reading Association.

Moyer, E. L., & Galindo, J. (2022). Achievement Level Description Review for the National Assessment of Educational Progress Mathematics and Reading Assessments. Final Process Documentation and Technical Report. *National Assessment Governing Board.*

National Reading Panel, (2000). *Report of the National Reading Panel: Teaching Children to Read Findings and Determinations of the National Reading Panel by Topic Area.* Washington, DC: U.S. Government Printing Office.

Nelson, J. M. & Manset-Williamson, G. (2006). The impact of explicit, self-regulatory reading comprehension strategy instruction on the reading-specific self-efficacy, attributions, and affect of students with reading disabilities. *Learning Disability* Quarterly, 29(3),213-230. Retrieved from http://www.jstor.org/ stable/30035507. Accessed: 17/11/2014 10:24

Praneetponkrang, S., & Phaiboonnugulkij, M. (2014). The use of retelling stories technique in developing English speaking ability of grade 9 students. *Advances in Language and Literary Studies*, *5*(5), 141-154.

Pressley, M. (2000). what should comprehension instruction be the instruction of? In M. L. kamli, P.B. Mosenthal, P.D. Pearson, & R. Barr (eds.) *Handbook of Reading Research.* Lawrence Erlbaum Associates, New Jersey.

Regis-Onuoha, A. (2021). The effectiveness of story retelling on junior high school students' reading comprehension and writing. *African Journal of Social Issues*, *4*(1), 48-62.

Rhodes, L.K., & Shanklin, N.L. (1993). *Windows into literacy*: Assessing learners, K–8. Portsmouth, NH: Heinemann.

Risonar, C. J., Digamon, J., De La Pena, J., & Delima, R. R. (2021). Story Retelling (SR) Technique in Improving Reading Comprehension of Sixth-Graders. *JPAIR Multidisciplinary Research*, *46*(1), 107–129. https://doi.org/10.7719/jpair.v46i1.453

Rudiawan & Jupri (2020) . Retelling strategy towards students' english reading comprehension at senior high schools. *JOLLT Journal of Languages and Language Teaching* . DOI: https://doi.org/10.33394/jollt.v8i4.2815

Samsudin, S., & Sukrisno, A. (2016). Improving Studentsâ€™ Motivation In Speaking Ability By Using Story Retelling. *English Education Journal*, *6*(2), 1-9.

Schisler, R., Joseph, L. M., Konrad, M., & Alber-Morgan, S. (2010). Comparison of the effectiveness and efficiency of oral and written retelling and passage review as strategies for comprehending text. *Psychology in the Schools, 47* (2), 135-152. Doi:10.1002/pits.20460.

Schisler, R.A.(2008). *Comparing the Effectiveness and Efficiency of Oral and Written Retellings for Improving Reading Comprehension Performance.* [Unpublished manuscript]The Ohio State University.

Souriyavongsa, T., Rany, S., Abidin, M. J. Z., & Mei, L. L. (2013). Factors causes students low English language learning: A case study in the National University of Laos. *International journal of English language education*, *1*(1), 179-192.

Suriani, S., & Yeni, M. (2023). Retelling as a Strategy in Enhancing Students' Reading Comprehension of Recount Text; A Classroom Action Research. *Edukasi*, *11*(2), 156-165.

Taylor, B.M. (1982). A Summarizing Strategy to Improve Middle Grade Students Reading and Writing Skills. *The Reading Teacher, 37*, 161-65.

Trisnawati,L.(2017).The effect of retelling technique on readingcomprehension at the eleventh grade of ma ma'arif pare academic year 2016/2017. *Simki-Pedagogia Vol. 01 No. 02 Tahun 2017 ISSN : AAAA-AAAA.*

Tsehay Jemberu (2013) Reading assessment of early grade children of five woredas in North Gonder of Amhara Region.A baseline data analytic report; save the children,Norway.

Wittrock, M. C. (1974). Learning as a generative process. *Educational Psychologist, 11*, 87-95.. doi:10.1080/ 00461520903433554.

Wittrock, M. C. (1981). Reading comprehension . In F. J. Pirozzolo & M. C. Wittrock (Eds.), Neuropsychologica l and cognitive processes in reading .*Reading Research Quarterly,* New York.

Yu-Ling, S. L., & Linan-Thompson, S. (2022) Teaching Description Structure of Expository Texts to Third Grade Students with Learning Disabilities. *International Journal of Arts, Humanities & Social Science* ISSN 2693-2547 (Print), 2693-2555 (Online) Volume 03; Issue no 04: April, 2022